# መቆጣት ያቃተው ወይስ ቁጣውን ወደ ተግባር መለወጥ የተሳነው ሕዝብ

በሀገራችን የተለመደው በደስታም ይሁን በሀዘን አብሮነት ነበር:: እኒህ የፎቶ መረጃዎች ግን የሚያመለክቱት አስተዛዛኝም ጭምር የጠፋበትና ልጅን በብርድልብስ ጠቅልሎ ብቻውን ወደ ቀብር መሄድን ነው። ይህ ዝነኛውና አረንጓዴው ረሀብ በመባል የሚታወቀውና በተለይ በደቡብ ክልል ያለውን ሕዝብ እያጠፋ ያለው ምርት አልባነት ነው። በለምለሙ መስክ ላይ የእህል ክምር ሳይሆን የሕጻናት ሬሳ የሚቆለልበት የአገራችን ክፍል መሆኑ ነው።



ልጆቹን በቀረችው ብርድልብስ ገንዞ ብቻውን የሚቀብር ሕዝብ ነው የትግራይ ልጆችን ለማስተማር ይሆን ዘንድ ለትምህርት ቤታቸው ማሰርያ ገንዘብ የሚያበረክተው። የትግራይ ልጆች ሲማሩ የደቡብ ሕጻናት በረሀብ እየረገፉ ለአረብ ቱጃር ለሚሸጡ መሬቶች ማዳበርያ ይሆናሉ።

ገበያ ደርሰው እንደሚመለሱ ሴት ወይዘሮ ምናልባትም የልጅ ልጃቸውን ሊሆን ይችላል ሬሳ ተሸክመው ብቻቸውን ያዘግማሉ። ከዐይናቸው ሊፈስ የሚችል እንባ የለም። በዝምታ በዝግታ ያዘግማሉ። ይህ እድርና ዘመድ አዝማድ ላለባት ኢትዮጵያውያ የተለመደ እይታ አልነበረም። ነገር ግን ሞት የተለመደ ነገር ሆኖአል። ኑሮውም የሞት እኩሌታ ነው ስለዚህ ባሸለቡና በሞቱ ሕጻናት መሀል መሆን ግድ ነው።



አሁን አሥራ አራት ሚልዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ በከፍተኛ ረሀብ ላይ ይገኛል። ገዢዎቻችን ረሀብ የለም ሲሉ ከተቀረው የአገሪቱ ክፍል እያግበሰበሱ በሚወስዱት የትግራይ ክልል ጎተራ ልክ በመሆኑ እነርሱ እንደ ሰው የማይቆጥሩትን ተራብ ሊሉ ኅሊናቸው አልፈቀደም። አንዳንዴም የገንዘብ ማስገኛ ስለሚሆን ብቻ ነው ረሀብ መኖሩን መናገር የሚሹት። የነገሩን አደገኛነትና የትግራይን ሕዝብ እንደ አጥር የመጠቀም ካልሆነ በቀር ወያኔዎች ለትግራይ ሕዝብም ደንታ የላቸውም። ባያድላቸው እንጂ ኤርትራዊነት የሚቀናቸው ነበሩ። ለትግራይ ሕዝብ አስባለሁ የሚል መሪ ይህን አይነት አጥፊ ፖሊሲ ይኖረዋል የሚል ማን ነው? የመገንጠልም ነገር እንኳ እውነት ቢሆን ምን አይነት ጉርብትና ለመፍጠር? በምን ራዕይ በምን እሳቤ እንዲህ ያለ ግፍ ይፈጸማል? ሽፍቶቹ ቀን ዘንበል ሲል የትግራይን ሕዝብ እሳት ጨምረውት ቢሄዱ ደንታ የላቸውም። ይህን ልብ ያላሉ የትግራይ ሆዳሞችና ሌሎች ፍርፋሪ ለቃሚዎች ግን ሬሳ ስጥን ውስጥ ጋደም ብለው ሞት የመጠበቅ ያህል የሆነውን ግብዝነታቸውን የተረዱት አይመስልም።



በእርግጥ ይህ ሁሉ ሲሆን ታድያ እብሪተኛ ወያኔዎችን ተሸክሞ ለመኖር የሰዉ ኅሊና እንዴት ፈቀደ? ሰዉ መቆጣት ስላቃተው ወይንስ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አስተሳሰብ የሃያ አንደኛውን ክፍለ ዘመን ፖለቲካ ማራመድ የሚሹ የፖለቲካ ድርጅቶች እየተፍረከረኩበት? ሁሉም በራሱ አእምሮ ውስጥ ከኔ ወዲያ ለአሳር የሚልና የሚፈጥረው ሕብረት ይህን ህልሙን እስካልተፈታተነ ድረስ ብቻ እየሆነ በየወንዙ ሲማማል? ወይስ አቦይ ስብሀት እንዳሉት መሸነፋን ተቀብሎ ለወያኔዎች ሰግዶ ለመኖር የፈቀደ ሕዝብ ሆኖ? ወይስ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አምረረን እንታገለዋለን ከሚሉት ተናንቀው ሳይሆን እርስ በርስ ተባልተው እርሱንም እያስበሉ ተስፋ እያስቆረጡት?



አሁን እንዲህ ሬሳ ታቅፎ ለሚጓዝ ሕዝብ እኔ ካልመራሁህ ቢሉት ምን ኩራት ሊገኝ ምንስ ክብር ሊታፈስ? ይህን በአንክሮ ስንመለከት በእውነት የኢትዮጵያ ሕዝብ መቆጣት ነው ያቃተው ወይስ ቁጣውን ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚያስችለው የጀርባ አጥንቱ በአሉባልታ የማይሚሸሽና ራሱን እየጠለፈ ለመጣል የማይጣደፍ ጠንካራ ድርጅት?

ጀግና በጭንቅ ቀን እንዲወለድ ሁሉ የዚህን ሁሉ የከፋት ምንጭ የሚደፍን ከሥልጣን በፊት ነጻነት የሚል ድርጅት ይኖረን ዘንድ እርግጥ ነው። ብዙ ዐይኖች ደግሞ ወደ ግንቦት ሰባት ያማትራሉ።

**ምስጋና፦ የሀሳቡ መነሻ ለሆኑ የኢትዮጵያ ከረንት አፌየርስ የመወያያ መድረክ ታዳሚዎች**
**ፎቶግራፎቹ Ethiopia's Harvest of Hunger ከሚል የታይምስ ድህረ ገጽ የተወሰዱ ናቸው**
http://www.time.com/time/photogallery/0,29307,1829664_1745853,00.html
ዳኛቸው ቢያድግልኝ